# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# መስተዳድር ምክር ቤት

# የፕሮጀክት መደልደያ ቀመር መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 18/2018 ዓ.ም

# መመሪያ ቁጥር 18/2018 ዓ.ም

# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፕሮጀክት መደልደያ ቀመር መስተዳድር ምክር ቤት መመሪያ

የልማት ፕሮጀክቶች የክልሉን ፈጣን የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ዕድገት ተግባራዊነት በዘላቂነት ለማረጋገጥ፤ የህዝቡን ተጠቃሚነት ከፍ ለማድረግ እና ሁሉን አቀፍ ዕድገትን ለማጎናጸፍ የሚያስችሉ ሆነው እንዲቀረጹ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

ፕሮጀክቶች ከፍትሃዊነት በተጨማሪ ጥራታቸው ተጠብቆ ውጤታማ እንዲሆኑ በማድረግ የዘላቂ የልማት እድገትን ለማረጋገጥ መሰረት ሆነው እንዲገነቡ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የልማት ፕሮጀክቶችን በፍትሃዊነትና በእኩልነት ተግባራዊ በማድረግ የህዝብ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ፣ ንግድ ኢንቨስትመንትን ለማሳለጥ፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሻሻል፣ የንጹህ መጠጥ ውሃና የንፅህና አጠባበቅ አቅርቦትን ለማረጋገጥ፣ መልካም አስተዳደር ለማስፈን እንደሚያስችል በመታመኑ፤

ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በክልሉ መንግስት በጀት ለሚገነቡ ፕሮጀክቶች ደረጃውን የጠበቀ የፕሮጀክቶች ቀመር በማዘጋጀት በምክንያታዊነት እና ውጤታማ በሆነ አግባብ የፕሮጀክት ልማት የሚስፋፋበትን ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ተገቢነቱ ስለታመነበት፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የፕሮጀክት መደልደያ ቀመር መስተዳድር ምክር ቤት መመሪያ ቁጥር 18/2018 ዓ/ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1/ **“ምክር ቤት”** ማለት የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት እና የየርከኑን አስተዳደር ምክር ቤቶችን ይጨምራል፤

2/ **“የፕሮጀክት በጀት”** ማለት በክልሉ ውስጥ ለልማት ፕሮጀክቶች የተመደበ ሀብት ነው፤

3/ **“የፕሮጀክት መደልደያ ቀመር”** ማለት ወሳኝ የሆኑ የፕሮጀክት አይነቶችን በመለየት ፍትሐዊነትን እና ውጤታማነትን በማረጋገጥ ቅድሚ የሚሰጥበት ሥርዓት ነው፤

4/ **“የቆዳ ስፋት”** ማለት የአስተዳደር እርከኖች በሕግ አግባብ ተለይቶ የሚያስተዳድሩት የተከለለ የአስተዳደር ወሰን በስኩየር ኪ.ሜ ወይም በሄክታር የሚገለፅ የአስተዳደር አካባቢ ነው፤

5/ **“የሕዝብ ብዛት”** ማለት በአንድ የተወሰነ አካባቢ የሚኖር ጠቅላላ የሰው ቁጥር ነው፤

6/ **“የሕዝብ ጥግግት”** ማለት በአንድ የተወሰነ አካባቢ በአንድ ካሬ ኪሎ ሜትር በአማካይ የሚኖሩ የሰዎች ብዛትን የሚመለከት ነው፤

7/ **“የመንገድ ጥግግት”** ማለት በአንድ የተወሰነ አካባቢ በአንድ ካሬ ኪሎ ሜትር ያለው ጠቅላላ የመንገድ ርዝመት ነው፤

8/ **“የአየር ላይ ራዲዩስ ልኬት”** ማለት በመስፈርቱና በስታንዳርዱ መሰረት ከአንድ ከተማ ማዕከል ተነስቶ በሚጠይቀው ልኬት መሰረት በአየር ላይ የመለካት ዘዴ ነው፤

9/ **"በጦርነት ምክንያት የተደረሰ ጉዳት"** ማለት በጦርነቱ ምክንያት በክልላችን የደረሰ ሰብዓዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና አካባቢያዊ ጉዳት ነው፤

10/ **"መልሶ ማገገም"** ማለት በጦርነቱ ወይም በግጭቱ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸዉን አካባቢዎችና ተጎጅዎችን በአጭር ጊዜ ዉስጥ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ በማድረግ አገልግሎቶችን ማስጀመር ነዉ፤

11/ "**መልሶ መገንባት**" በግጭቱ ወይም በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸዉን አካባቢዎችና ተጎጅዎችን ከረጅም ጊዜ አኳያ ድጋፍና እገዛ በማድረግ የአሁንና የወደፊት ፍላጎታቸዉን ማማላት የሚያስችሉ ግንባታዎችን ማካሄድ ነዉ፤

12/ "**መልሶ ማልማት**" በግጭቱ ወይም በጦርነቱ የተጎዱትን አካባቢዎችና ህዝብ በተሟላ መንገድ ሙሉ በሙሉ ወደነበሩበት የመመለስና ዘላቂ ልማትን ማምጣት ነዉ፤

13/ "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

14/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸ ሁሉ ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአማራ ክልል ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በክልሉ መንግስት በጀት በሚገነቡ ፕሮጀክቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማ

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1/ ጥራት ያላቸውን ፕሮጀክቶች በመገንባት ውጤታማ እና ዘላቂ የልማት እድገትን ማረጋገጥ፤

2/ በክልሉ የሚገኙ የተለያዩ የልማት ፀጋዎችን ለክልሉ ሕዝብ የጋራ ጥቅም ማበልፀግ፤

3/ የክልሉን ፈጣን ኢኮኖሚ እና ማኀበራዊ ዕድገት በማፋጠን የሕዝብን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡፡

## 5. መርሆዎች

የፕሮጀክቶች ድልድል ቀመር የሚከተሉትን መርሆዎች በመከተል የሚፈጸም ይሆናል፡-

1/ ውጤታማነት፤

2/ ፍትሃዊነት፤

3/ አሳታፊነት፤

4/ የህዝብ ተጠቃሚነት፤

5/ ተጠያቂነት ፡፡

# ክፍል ሁለት

# የፕሮጀክት መደልደያ ቀመር መስፈርቶች

## 6. የፕሮጀክት መደልደያ ቀመር መመዘኛ መስፈርቶች

በክልሉ ፕሮጀክት ቀመር ድልድል ለማድረግና ለመወሰን እንደየተቋማቱ የሚለያዩ ቢሆንም የሚከተሉት መመዘኛዎች እንደየፕሮጀክቶችና ተቋማት አግባብነት በሥራ ላይ ይውላሉ፡-

1/ የሕዝብ ብዛት፣

2/ የህዝብ አሰፋፈር ጥግግት፣

3/ የሚያስተናግዷቸው የተማሪዎች ብዛት፤

4/ የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት፤

5/ የቆዳ ስፋት፤

6/ የህመምና የሞት ምጣኔ፤

7/ የመሬት አቀማመጥና የአየር ንብረት አይነቶች፤

8/ የመሰረተ ልማት ተጠቃሚነት፤

9/ ለኢኮኖሚ ዕድገት ያለው አበርክቶ፤

10/ ለሶሾዮ-ኢኮኖሚ ያለው አበርክቶ፤

11/ የመንገድ ጥግግት፤

12/ የውኃ ሽፋን፤

13/ የአካባቢ ጅኦሎጂ፤

14/ የማህበረሰብ ተሳትፎ፤

15/ የውሀ ተቋማት የብልሽት ምጣኔ፤

16/ የውሀ ምርትና የውሀ ብክነት ምጣኔ፤

17/ በመስኖ መልማት የሚችል መሬት እና ውኃ፤

18/ የስራ እድል ፈጠራ፤

19/ የድርቅ ተጋላጭነት፤

20/ ዘላቂ የምርት ግብዓት አቅም፤

21/ ማዕከላዊነት፤

22/ የመሬት አቅርቦት፤

23/ ሰላማዊና ማህበራዊ ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ፤

24/ የሰው ሀይል አቀርቦት፤

25/ የእንስሳት ብዛት እና የዓሳ እምቅ ሀብት፤

26/ ከእንስሳት የሚገኙ ምርቶች፤

27/ የእንስሳት መኖ አቅርቦት፤

28/ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ማሻሻል፤

29/ የቅርሱ ወይም መስህቡ ወይም መዳረሻው ልዩ ገጽታና ዋጋ፣

30/ የቅርሱ ወይም መስህቡ ወይም መዳረሻው በዙሪያው ያሉ የለሙና ወደፊት መልማት የሚችሉ ቅርሶች ብዛት፤

31/ ለሁሉም የመሰረተ-ልማት አይነቶች ያለው ቅርበትና የመተሳሰር አመቺነት፤

32/ የአማራ ክልል በጦርነቱ የተጎዱ አካባቢዎች መልሶ ማቋቋምና ግንባታ መስፈርቶች፤

33/ በመስተዳድር ምክር ቤት ውሳኔ የሚገነቡ ፕሮጀክቶች።

## 7. የትምህርት ተቋማት መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች መስፈርት

1/ የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮጀክት መመዘኛ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፦

ሀ) የሚያስተናግዷቸው ተማሪዎች ብዛት፣

ለ) የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት፣

ሐ) የመሠረተ ልማት ተጠቃሚነት እና፤

መ) የህዝብ አሰፋፈር ጥግግት ናቸው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሀ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚያስተናግዷቸው ተማሪዎች መስፈርት 50 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን የተማሪዎች ብዛት፦

ሀ) ለቅደመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 180 ዕድሜያቸው ከ4-6 ዓመት የሆናቸው፤

ለ) ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት 2000 ዕድሜያቸው ከ7-14 ዓመት የሆናቸው እና፤

ሐ) ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 3000 ዕድሜያቸው ከ15-18 ዓመት የሆናቸው ይሆናል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ሀ የተገለጸው የቅደመ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመገንባት የሚያስተናግዱቸው ተማሪዎች ብዛት የሚያስገኘውን መስፈርት ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = \left\{\frac{\text{ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ}(4-6)\text{ ዓመት}) - \text{እየተማሩ ያሉ ተማሪዎችብዛት}}{\text{ለመስፈርቱ }(180)}\right] * \text{ለነጥቡ ክብደት}(50\%)$$

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ለ የተገለጸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመገንባት የሚያስተናግዷቸው ተማሪዎች ብዛት የሚያስገኘውን መስፈርት ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = 3 * \left\{\frac{\text{ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ}(7-14)\text{ ዓመት}) - \text{እየተማሩ ያሉ ተማሪዎችብዛት}}{\text{ለመስፈርቱ }(2{,}000)}\right]$$

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ሐ የተገለጸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመገንባት የሚያስተናግዷቸው ተማሪዎች ብዛት የሚያስገኘውን መስፈርት ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = 3 * \left\{\frac{\text{ዕድሜያቸው ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤት የደረሰ}(15-18)\text{ ዓመት}) - \text{እየተማሩ ያሉ ተማሪዎችብዛት}}{\text{ለመስፈርቱ }(3{,}000)}\right]$$

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ለ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት መስፈርት 30 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ ኪሎ ሜትሩም ለቅደመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ1 ኪሎ ሜትር የማይበልጥ፣ ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ2 ኪሎ ሜትር የማይበልጥ እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ3 እስከ 5 ኪሎ ሜትር ያልበለጠ መሆን አለበት፤

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተገለጸው የቅደመ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመገንባት የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = 100 * [\left\{\frac{\text{የቆዳ ስፋት} - \text{ተጠቃሚ የሆኑት የቆዳ ስፋት (ነባር ት.ቤቶች በ1 ኪ.ሜትር ራዲየስ)}}{\text{የቆዳ ስፋት (ኪ.ሜ}^2)}\right] * \text{ለነጥቡ ክብደት}$$

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተገለጸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመገንባት የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = 100 * [\left\{\frac{\text{የቆዳ ስፋት} - \text{ተጠቃሚ የሆኑት የቆዳ ስፋት (ነባር ት.ቤቶች በ2 ኪ.ሜትር ራዲየስ)}}{\text{የቆዳ ስፋት (ኪ.ሜ}^2)}\right] * \text{ለነጥቡ ክብደት }(30\%)$$

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተገለጸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመገንባት የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = 100 * [\left\{\frac{\text{የቆዳ ስፋት} - \text{ተጠቃሚ የሆኑት የቆዳ ስፋት (ነባር ት.ቤቶች በ3 ኪ.ሜትር ራዲየስ)}}{\text{የቆዳ ስፋት}}\right] * \text{ለነጥቡ ክብደት }(30\%)$$

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሐ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመሰረተ-ልማት መስፈርት ለቅደመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የመሬት አቀማመጥ፣ ለትራፊክ አደጋ የማያጋልጥ፣ በቀላሉ ንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚገኝበት፣ ከዋና መንገድ እስከ 100 ሜትር ገባ ያለ፣ በአቅራቢያው የጤና ተቋማት ያለው፣ ተላላፊ በሽታ ከሚያመጡ እና በድምጽ ከሚረብሹ ድርጅቶች 500 ሜትር የራቀ ሆኖ አጠቃላይ መስፈርቱ 10 በመቶ ነጥብ የተሰጠው ሲሆን ከዚህ ውስጥ፦

ሀ) ከውሃማ አካላት ያለው ርቀት 3% ነጥብ፣

ለ) ለትራንስፖርት ያለው ቀረቤታ 4% ነጥብ እና፤

ሐ) ምቹ መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ 3% ነጥብ ክብደት የሚይዙ ይሆናል።

11/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሐ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመሰረተ-ልማት መስፈርት ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሁሉም ተማሪዎች በቀላሉ ሊደርሱበት በሚችሉ ቦታዎች በተለይ የአካል ጉዳተኞችን እና ከርቀት አካባቢዎች ተመላልሰው ለሚማሩ ሴት ተማሪዎችን ታሳቢ ያደረገ ሆኖ አጠቃላይ መስፈርቱ 10 በመቶ ነጥብ የተሰጠው ሲሆን ከዚህ ውስጥ፦

ሀ) ከውሃማ አካላት ያለው ርቀት 3% ነጥብ፣

ለ) ለትራንስፖርት ያለው ቀረቤታ 4% ነጥብ እና፤

ሐ) ምቹ መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ 3% ነጥብ ክብደት ይይዛሉ።

12/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሐ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመሰረተ-ልማት መስፈርት ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመገንባት ለመኪና መንገድ ያለው ቅርበት፤ ከትራፍፊክ መጨናነቅ ያልተጋለጠ፣ ከመጠጥ ቤቶች፣ ለሱስ ከሚዳርጉ ቦታዎች፣ ከገበያ ቦታዎች የራቀ፣ ወንዞች፣ ሀይቆችና ወጣ ገባ ያልበዙበት ቦታ ሆኖ አጠቃላይ መስፈርቱ 10 በመቶ ነጥብ የተሰጠው ሲሆን ከዚህ ውስጥ፦

ሀ) ከውሃማ አካላት ያለው ርቀት 3% ነጥብ፣

ለ) ለትራንስፖርት ያለው ቀረቤታ 4% ነጥብ እና፤

ሐ) ምቹ መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ 3% ነጥብ ክብደት ይይዛሉ።

13/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ መ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የህዝብ አሰፋፈር ጥግግት መስፈርት ሁሉንም ትምህርት ቤቶች ለመስራት በተመሳሳይ ሁኔታ የህዝብ አሰፋፈር ጥግግት መታየት የሚኖርበት ሲሆን ይህም ህዝብ በከፍተኛ ደረጃ ያለባቸው አካባቢዎች በቁጥር

በርካታ ተማሪዎች ይኖራሉ ተብሎ ስለሚታሰብ መስፈርቱ 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚይዝ ይሆናል፤

14/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13 የተገለጸው የህዝብ አሰፋፈር ጥግግት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$ጥብ = 0.3 * [\left\{\frac{የህዝብ\ ብዛት}{የቆዳ\ ስፋት(ኪ.ሜ^2)}\right] * ለነጥቡ\ ክብደት(10\%)$$

15/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 14 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለቅድመ አንደኛ እና ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአራቱ መስፈርቶች ድምር ውጤት 70 በመቶና ከዚያ በላይ እንዲሁም ለሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤቶች ድምር ውጤት 60 በመቶና ከዚያ በላይ ሲያሟላ የጠየቀው አካል በአገኘው የነጥብ ደረጃ ፕሮጀክቱን በቅድሚያ የሚያገኝ ሲሆን ውጤቱ ከዚህ በታች ከሆነ በአገኘው ውጤት ደረጃ መሰረት እንደቅደም ተከተሉ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

## 8. የጤና ተቋማት መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች

1/ ለሆስፒታል ፕሮጀክት መመዘኛ መስፈርቶች፦

ሀ) የህዝብ ብዛት፣

ለ) የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት፤

ሐ) የህመምና የሞት ምጣኔ እና፤

መ) የህዝብ አሰፋፈር ጥግግት ናቸው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሀ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የህዝብ ብዛት መስፈርት 75 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ በሃገር አቀፍ የጤና ፖሊሲ ስታንዳርድ መሰረት፦

ሀ) አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ለ80,000 ሰዎች፤

ለ) አንድ ጠቅላላ ሆስፒታል ለ1,250,000 ሰዎች እና፤

ሐ) አንድ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለ4,000,000 ሰዎች አገልግሎት እንደሚሰጡ ታሳቢ ተደርጎ መሰራት አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ሀ እስከ ሐ የህዝብ ብዛት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$ነጥብ = [45 * \{የሚያስፈልገው\ ሆስፒታል - ነባር\ ሆስፒታል]] * ለነጥቡ\ ክብደት(75\%)$$

$$ስሌቱም\ የሚያስፈልገው\ ሆስፒታል = \left\{\frac{የህዝብ\ ብዛት}{ለሆስፒታል\ መስፈርቶቹ}\right.$$

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ለ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ፦

ሀ) የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች 30 ኪሎ ሜትር፤

ለ) ጠቅላላ ሆስፒታል 60 ኪሎ ሜትር እና፤

ሐ) ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል 90 ኪሎ ሜትር እንዲሸፍኑ ተደርጎ መሰራት አለበት፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የተገለጸው የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$ነጥብ = [100 * \left\{\frac{የቆዳ\ ስፋት - ተጠቃሚ\ የሆኑት\ የቆዳ\ ስፋት\ (ነባር\ ሆስፒታሎች\ በመስፈርቶቹ\ ኪ.ሜትር\ ራዲየስ)}{የቆዳ\ ስፋት}\right.]] * ለነጥቡ\ ክብደት\ (10\%)$$

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ከፊደል ተራ ሀ እስከ ሐ የተገለጸው ቢኖርም ነባር ሆስፒታሎች በራዲየስ ልኬት በሚካተቱ አካባቢዎች ካሉ በዚህ መስፈርት መሰረት ተጨማሪ የሆስፒታሎች አይገነቡም፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሐ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የህመምና የሞት ምጣኔ መስፈርት 5 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ አመላካቾችም የሚከተሉት ናቸው፦

ሀ) ከአጠቃላይ ማህበረሰብ ውስጥ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መጠን፤

ለ) የጤና አገልግሎት ያገኙ እናቶች እና ህጻናት፤

ሐ) በሁሉም አይነት በሽታ የተመዘገበ ህመም፣

መ) በሁሉም አይነት በሽታ የተመዘገበ ሞት፣

ሠ) በተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ያገኙ ሰዎች ብዛት፤

ረ) ተኝተው የታከሙ ሰዎች ብዛት፣

ሰ) የቀዶ ጥገና አገልግሎት ያገኙ ሰዎች ብዛት እና፤

ሸ) የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ያገኙ ሰዎች ብዛት፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ መ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የህዝብ አሰፋፈር ጥግግት መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን አመላካቾችም፦

ሀ) የተበታተነ አሰፋፈር ያለቸው አካባቢዎች፤

ለ) የተሻለ የጤና ተቋማት ስርጭት አለመኖር፤

ሐ) የረጅም ጊዜ የጤና ፕሮግራሞች ለማከናወን እና፤

መ) ከርቀት አካባቢ የሚመጡ ማህበረሰቦች ታሳቢ ማድረግ ናቸው፤

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 የተገለጸው የህዝብ አሰፋፈር ጥግግት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$ነጥብ = 10 - [0.3 * [\{\frac{የህዝብ ብዛት}{የቆዳ ስፋት}] * ለነጥቡ ክብደት (10\%)]$$

10/ ለጤና ጣቢያ እና ጤና ኬላ ፕሮጀክት መመዘኛ መስፈርቶች፦

ሀ) የህዝብ ብዛት፣

ለ) የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት ናቸው።

11/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10 ፊደል ተራ ሀ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የህዝብ ብዛት መስፈርት 80 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ በሃገር አቀፍ የጤና ፖሊሲ ስታንዳርድ መሰረት፦

ሀ) አንድ ጤና ጣቢያ ለ20,000 ሰዎች እና አምስት ጤና ኬላዎችን በጋራ በማቀፍ፤

ለ) አንድ ጤና ኬላ ለ4,000 ሰዎች እና ጤና ጣቢያ በሌለባቸው ቀበሌዎች ቢያንስ አንድ ጤና ኬላ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጎ መሰራት አለበት፡፡

12/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11 ፊደል ተራ ሀ የጤና ጣቢያ የህዝብ ብዛት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፦

$$ነጥብ = [25 * \{የሚያስፈልገው ጤና ጣቢያ - ነባር ጤና ጣቢያ ]] * ለነጥቡ ክብደት(80\%)$$

$$ስሌቱም \quad የሚያስፈልገው ጤና ጣቢያ = \{\frac{የህዝብ ብዛት}{ለመስፈርቱ (20,000)}$$

13/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11 ፊደል ተራ ለ የጤና ኬላ የህዝብ ብዛት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$ነጥብ = [20 * \{የሚያስፈልገው ጤና ጣቢያ - ነባር ጤና ጣቢያ ]] * ለነጥቡ ክብደት(80\%)$$

$$ስሌቱም \quad የሚያስፈልገው ጤና ጣቢያ = \{\frac{የህዝብ ብዛት}{ለመስፈርቱ (4,000)}$$

14/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10 ፊደል ተራ ለ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት መስፈርት 20 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ፦

ሀ) አንድ ጤና ጣቢያ የመኳኳኘ ሁኔታ፣ የጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ እና የጤና አጠባበቅ ስርዓቱ አጠቃላይ አቅም ላይ በመመስረት 5 ኪሎ ሜትር እንዲሸፍን ተደርጎ መሰራት አለበት፡፡

ለ) አንድ ጤና ኬላ የመንገድ እና ትራንስፖርት ችግሮችን ለመቀነስ እና ቅድሚያ እንክብካቤና ምክር አገልግሎት ለመስጠት እንዲችል በ2 ኪሎ ሜትር ርቀት አገልግሎት መስጠት እንዲችል ተደርጎ መሰራት አለበት፡፡

ሐ) ህብረተሰቡ ከጤና ተቋማት ለመድረስ በመካከለኛ የእግር ጉዞ ከ30 ደቂቃ በታች ሲጓዝ መሰረታዊ ጤና ኬላ እና ከ1 ሠዓት በላይ ሲጓዝ ደግሞ አጠቃላይ ጤና ኬላ እንዲያገኝ ተደርጎ መገንባት አለበት፡፡

15/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ ሀ የጤና ጣቢያ የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = [100 * [\{\frac{\text{የቆዳ ስፋት} - \text{ተጠቃሚ የሆኑት የቆዳ ስፋት (ነባር ጤና ጣቢያ በ5 ኪ.ሜትር ራዲየስ)}}{\text{የቆዳ ስፋት}}]] * \text{ለነጥቡ ክብደት} (20\%)$$

16/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ ለ እና ሐ የጤና ኬላ የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = [100 * [\{\frac{\text{የቆዳ ስፋት} - \text{ተጠቃሚ የሆኑት የቆዳ ስፋት (ነባር ጤና ኬላ በ2 ኪ.ሜትር ራዲየስ)}}{\text{የቆዳ ስፋት}}]] * \text{ለነጥቡ ክብደት} (20\%)$$

17/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 16 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች እና ጤና ኬላዎች መስፈርቶች ድምር ውጤት 70 በመቶና ከዚያ በላይ ሲያሟላ የጠየቀው አካል በአገኘው የነጥብ ደረጃ ፕሮጀክቱን በቅድሚያ የሚያገኝ ሲሆን ውጤቱ ከዚህ በታች ከሆነ በአገኘው ውጤት ደረጃ መሰረት እንደቅደም ተከተሉ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

## 9. <u>የውሀ ተቋማት መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች</u>

1/ ለገጠር ውሃ ፕሮጀክት መመዘኛ መስፈርቶች፦

ሀ) የህዝብ ብዛት፣

ለ) የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት፤

ሐ) የመሬት አቀማመጥና የአየር ንብረት ሁኔታ፣

መ) የአከባቢው ጂኦሎጂ፤

ሠ) የማህበረሰቡ ተሳትፎ እና፤

ረ) የውሃ ተቋማት የብልሽት ማጣኔ ናቸው፡፡

2/ ለከተማ ውሃ ፕሮጀክት መመዘኛ መስፈርቶች፦

ሀ) የህዝብ ብዛት፣

ለ) የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት፤

ሐ) የመሬት አቀማመጥና የአየር ንብረት ሁኔታ፣

መ) የአከባቢው ጂኦሎጂ

ሠ) የማህበረሰቡ ተሳትፎ፤

ረ) የውኃ ምርት ምጣኔ እና፤

ሰ) የውኃ ብክነት ምጣኔ ናቸው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሀ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለገጠር ውሃ ፕሮጀክቶች የህዝብ ብዛት መስፈርት 50 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ፦

ሀ) ምንጭ በቦታዉ ባለ አንድ መውጫ ለ180 ሰዎች፤

ለ) የእጅ ጉድጓድ መደበኛ ፓምፕ የተገጠመለት ለ180 ሰዎች፤

ሐ) መለስተኛ ጥልቅ ጉድጉድ ፖምፕ የተገጠመለት ለ250 ሰዎች፤

መ) ምንጭ ከነማከፋፈያው አንድ ቦኖ ባለ ስድስት ፎሴት ለ900 ሰዎች፤

ሠ) በሞተር ሃይል ወይም በመሬት ስበት የሚሠራ ፓምፕ ያለው ጥልቅ /መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ/ ዋና መስመር፣ ማሰራጫ መስመር፣ ማጠራቀሚያ ጋንና ከአንድ በላይ ቦኖ ስድስት ፎሴት ያለዉ አንድ ቦኖ ለ900 ሰዎች አገልግሎት እንደሚሰጡ ታሳቢ ተደርጎ መሰራት አለበት፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ ሀ እስከ መ ለገጠር ውሃ ፕሮጀክት የተገለጸው የህዝብ ብዛት ነጥብ ክብደትና መስፈርት ለከተማ ውሃ ፕሮጀክቶች በተመሳሳይ የሚያገል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሞተር ሃይል ወይም በመሬት ስበት የሚሠራ ፓምፕ ያለው ጥልቅ /መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ/ ዋና መስመር፣ ማሰራጫ መስመር፣ ማጠራቀሚያ ጋንና ከአንድ በላይ ቦኖ ስድስት ፎሴት ያለዉ ለ500 ሰው አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጎ መሰራት አለበት፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ሀ እስከ ሠ እና ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው የህዝብ ብዛት ነጥብ ክብደት ዝርዝር ስሌቱ፦

ሀ) የውኃ ሽፋን (በመቶኛ) ከ50 በታች…………..50 ነጥብ፤

ለ) የውኃ ሽፋን (በመቶኛ) ከ50.01 እስከ 60…….40 ነጥብ፤

ሐ) የውኃ ሽፋን (በመቶኛ) ከ60.0 እስከ 70……..30 ነጥብ፤

መ) የውኃ ሽፋን (በመቶኛ) ከ70.01 እስከ 80……20 ነጥብ፤

ሠ) የውኃ ሽፋን (በመቶኛ) ከ80.01 እስከ 90……10 ነጥብ፤

ረ) የውኃ ሽፋን (በመቶኛ) ከ90.01 እስከ 96……..5 ነጥብ፤

ሸ) የውኃ ሽፋን (በመቶኛ) ከ96 በላይ……0 ነጥብ፤ ይሆናል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ፊደል ተራ ሀ እስከ ፊደል ተራ ሸ የንፁህ መጠጥ ውሃ ተቋማትን ፕሮጀክት በጀት ለመደልደል የህዝብ ብዛት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$ነጥብ = 100 * \left\{\frac{በነባር\ መጠጥ\ ውሃ\ ተቋማት\ የተጠቃሚ\ ህዝብ\ ብዛት}{ጠቅላላ\ የህዝብ\ ብዛት}\right\}$$

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ለ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለገጠር ውሃ ፕሮጀክቶች የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት መስፈርት 20 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ የውሃ ተቋማት በተጠቃሚዎች እና በነባር የንፁህ መጠጥ ውሃ ተቋማት መካከል ያለው ርቀት፦

ሀ) የእጅ ጉድጓድ 1 ኪሎ ሜትር፤

ለ) ምንጭ በቦታዉ 1 ኪሎ ሜትር፤

ሐ) መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ 1 ኪሎ ሜትር፤

መ) ምንጭ ከነማከፋፈያው 1 ኪሎ ሜትር፤

ሠ) በሞተር ሃይል ወይም በመሬት ስበት የሚሠራ ፓምፕ ያለው ጥልቅ /መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ/ 0.5 ኪሎ ሜትር እንዲሸፍኑ ተደርጎ መሰራት አለበት፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 ፊደል ተራ ሀ እስከ ፊደል ተራ ሠ ለገጠር ውሃ ፕሮጀክት በተጠቃማዎችና በነባር የንፁህ መጠጥ ውሃ ተቋማት መካከል ያለው ርቀት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$ነጥብ = 100 * [\left\{\frac{የቆዳ\ ስፋት - ተጠቃሚ\ የሆኑት\ ማህበረሰቦች\ የቆዳ\ ስፋት}{የቆዳ\ ስፋት}\right\}] * ለነጥቡ\ ክብደት(20\%)$$

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ለ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለከተማ ውሃ ፕሮጀክቶች የአየር ላይ ራዲየስ ልኬት መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ የውሃ ተቋማት በተጠቃሚዎች መካከል ያለው ርቀት፦

ሀ) የእጅ ጉድጓድ 1 ኪሎ ሜትር፤

ለ) ምንጭ በቦታዉ1 ኪሎ ሜትር፤

ሐ) መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ 1 ኪሎ ሜትር፤

መ) ምንጭ ከነማከፋፈያው 1 ኪሎ ሜትር፤

ሠ) በሞተር ሃይል ወይም በመሬት ስበት የሚሠራ ፓምፕ ያለው ጥልቅ /መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ/ 0.25 ኪሎ ሜትር እንዲሸፍኑ ተደርጎ መሰራት አለበት፡፡

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 ፊደል ተራ ሀ እስከ ፊደል ተራ ሠ ለከተማ ውሃ ፕሮጀክቶች በተጠቃማዎችና በነባር የንፁህ መጠጥ ውሃ ተቋማት መካከል ያለው ርቀት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = 100 * [\{\frac{(\text{የቆዳ ስፋት} - \text{ተጠቃሚ የሆኑት ማህበረሰቦች የቆዳ ስፋት})}{\text{የቆዳ ስፋት}}] * \text{ለነጥቡ ክብደት}(10\%)$$

11/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሐ እና ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ሐ እንደቅደም ተከተሉ ለገጠርና ከተማ ውሃ ፕሮጀክቶች የመሬት አቀማመጠና የአየር ንብረት ሁኔታ መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ የመሬቱን ኮረብታማ፣ ተራራማ፣ ሜዳማ፣ ደረቃማ፣ ከፊል ደረቃማ እንዲሁም የድርቅ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን ትኩረት ተደርጎ መስራት አለበት፡፡

12/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ መ እና ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ መ እንደቅደም ተከተሉ ለገጠርና ከተማ ውሃ ፕሮጀክቶች የአካባቢው ጂኦሎጂ መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ የአፈር እና የድንጋይ ዓይነቶች፣ የከርሰ ምድር የውሃ መጠን እና ጥራት፣ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋን መለየት በሚያስችል መልኩ ታሳቢ ተደርጎ መስራት አለበት፡፡

13/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሠ እና ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ሠ እንደቅደም ተከተሉ ለገጠርና ከተማ ውሃ ፕሮጀክቶች የማህበረሰብ ተሳትፎ መስፈርት 5 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ አመላካቾችም፦

ሀ) ከፕሮጀክቱ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ አስተዳደራዊ ችግሮችን (የመሬት ካሣ ክፍያ፣ ትክ)፤ ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ መጋቢ መንገዶች ዝግጅት ለመፍታት ያላቸዉ ዝግጁነት፣

ለ) ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ተረክቦ ለማስተዳደርና ባለሙያዎችን ቀጥሮ ለማሰራት ያለዉ ዝግጁነት፤

ሐ) ከኅብረተሰቡ ጋር ዉይይትና ስምምነት ተደርጎ ቃለ ጉባዔ ከተያዘ በኋላ የወረዳዉ አስተዳዳሪ የማረጋገጫ ደብዳቤ ሲሰጥ እና የባንክ ሂሳብ ቁጥር ከፍተዉ ገንዘብ ማስቀመጥ የጀመሩ መሆኑ፤

መ) ማህበረሰቡ የጉልበት ድጋፍና ቁሳቁሶችን ለማቅረብ ያለው ዝግጁነት፤

14/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ረ ለገጠር ፕሮጀክቶች የውሃ ተቋማት የብልሽት ምጣኔ መስፈርት 5 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ ነባር የውሃ ተቋማትን በአግባቡ አገልገሎት እንዲሰጡ ማድረጋቸው እየተረጋገጠ መስራት አለበት፡፡

15/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 13 ላይ የተገለጸው የገጠር ውሃ ተቋማት የብልሽት ምጣኔ ዝርዝር ስሌት፦

ሀ) የብልሽት ምጣኔ (በመቶኛ) ከ10 በታች........5 ነጥብ፤

ለ) የብልሽት ምጣኔ (በመቶኛ) ከ10.01 እስከ 15....4 ነጥብ፤

ሐ) የብልሽት ምጣኔ (በመቶኛ) ከ15.01 እስከ 20....3 ነጥብ፤

መ) የብልሽት ምጣኔ (በመቶኛ ከ20.01 እስከ 25......1 ነጥብ፤

ሠ) የብልሽት ምጣኔ (በመቶኛ ከ25.01 በላይ......0 ነጥብ፤

16/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 15 ፊደል ተራ ሀ እስከ ፊደል ተራ ሠ የገጠር ውሃ ተቋማት የብልሽት ምጣኔ መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{የዉሃ ተቋማት የብልሽት ምጣኔ} = 100 * \left\{\frac{\text{አጠቃላይ የተገነቡ የዉሃ ተቋማት ብዛት} - \text{አገልግሎት የሚሰጡ የዉሃ ተቋማት ብዛት}}{\text{አጠቃላይ የተገነቡ የዉሃ ተቋማት ብዛት}}\right\}$$

17/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ረ ለከተማ ውሃ ፕሮጀክቶች የውሃ ተቋማት የውሃ ምርት ምጣኔ መስፈርት 5 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ መመረት ያለበት የውሃ መጠንን በአግባቡ መጠቀማቸው እየተረጋገጠ መስራት አለበት፡፡

18/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 17 ላይ የተገለጸው የከተማ ውሃ ተቋማት የውሃ ምርት ምጣኔ ዝርዝር ስሌት፦

ሀ) የውሃ ምርት ምጣኔ (በመቶኛ) ከ90 በላይ........5 ነጥብ፤

ለ) የውሃ ምርት ምጣኔ (በመቶኛ) ከ80.01 እስከ 90....4 ነጥብ፤

ሐ) የውሃ ምርት ምጣኔ (በመቶኛ) ከ70.01 እስከ 80....3 ነጥብ፤

መ) የውሃ ምርት ምጣኔ (በመቶኛ ከ60.01 እስከ 70......2 ነጥብ፤

ሠ) የውሃ ምርት ምጣኔ (በመቶኛ) ከ50.01 እስከ 60......1 ነጥብ፤

ረ) የውሃ ምርት ምጣኔ (በመቶኛ) ከ50 በታች...........0 ነጥብ፤ ይሆናል፤

19/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 18 ፊደል ተራ ሀ እስከ ፊደል ተራ ረ የከተማ ውሃ ተቋማት የውሃ ምርት ምጣኔ መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{የዉሃ ምርት ምጣኔ} = 100 * [\frac{\text{በአንድ አመት ዉስጥ መመረት ያለበት የዉሃ መጠን} - \text{በአንድ አመት ዉስጥ የተመርተ የዉሃ መጠን}}{\text{ጠቅላላ በአንድ አመት ዉስጥ መመረት ያለበት የዉሃ መጠን}}]$$

20/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ሰ ለከተማ ውሃ ፕሮጀክቶች የውሃ ተቋማት የውሃ ብክነት ምጣኔ መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ የውሃ ብክነት ገደብ፦

ሀ) ከ15.01 በታች....10 ነጥብ፣

ለ) ከ15.01-20....8 ነጥብ፣

ሐ) ከ20.01-25....6 ነጥብ፤

መ) ከ25.01-30....3 ነጥብ፤

ሠ) ከ30 በላይ....0 ነጠብ፤ የዉሃ ብክነት ገደብ በመቶኛ እየተሰላ እና ብክነትን በመቀነስ ተገቢውን አገልግሎት መስጠታቸው እየተረጋገጠ መስራት አለበት፡፡

21/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 20 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የውሀ ተቋማት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት ለመመደብ 6 ለገጠር እና 7 ለከተማ መስፈርቶች ድምር ውጤት 80 በመቶና ከዚያ በላይ ሲያሟላ የጠየቀው አካል በአገኘው የነጥብ ደረጃፕሮጀክቱን በቅድሚያ የሚያገኝ ሲሆን ውጤቱ ከዚህ በታች ከሆነ በአገኘው ውጤት ደረጃ መሰረት እንደቅደም ተከተሉ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

## 10. የመንገድ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች

1/ የመንገድ መሠረተ ለማት ፕሮጀክት መመዘኛ መስፈርቶች፦

ሀ) ፕሮጀክቱ ለኢኮኖሚ ዕድገት ያለው አበርክቶ፣

ለ) ፕሮጀክቱ ለሶሾዮ-ኢኮኖሚ ልማት ያለው አበርክቶ እና፤

ሐ) ፕሮጀክቱ በአካባቢው ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ናቸው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሀ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለመንገድ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት ፕሮጀክቱ ለኢኮኖሚ ዕድገት ያለው አበርክቶ መስፈርት 45 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ ዝርዝር ስሌቱም፦

ሀ) የግብርና ነገረ ምርት እምቅ አቅም.........................10 ነጥብ፣

ለ) የተመዘገቡ የቱሪዝም መዳረሻ................................10 ነጥብ፤

ሐ) የኢንዱስትሪ እምቅ አቅም......................................8 ነጥብ፤

መ) የተጠና ወይም የተመዘገበ እምቅ የማዕድን ሃብት..........7፤

ሠ) ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የኃይል ምንጭ..................5 ነጥብ እና፤

ረ) ከሌሎች መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ጋር ያለው ትስስር...5 ነጥብ ናቸው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ለ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለመንገድ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት ፕሮጀክቱ ለሶሾዮ-ኢኮኖሚ ልማት ያለው አበርክቶ መስፈርት 45 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ ዝርዝር ስሌቱም፦

ሀ) የአስተዳደር ሁኔታና የህዝብ ብዛት..............................7 ነጥብ፤

ለ) ግንኙነትና ክልላዊ ትስስር........................................6 ነጥብ፤

ሐ) የማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብዛት....................5 ነጥብ፤

መ) የመንገድ ጥግግት...................................................10 ነጥብ፤

ሠ) ድህነት ቅነሳ.........................................................5 ነጥብ፤

ረ) ለገበያ ትስስር ያለው አዎንታዊ ፋይዳ..............................3 ነጥብ፤

ሰ) ለስራ ዕድል ፈጠራ የሚሆን ፀጋና አማራጭ ያለው..............3 ነጥብ፤

ሸ) ለሰላምና ደህንነት ያለው ጠቀሜታ...............................3 ነጥብ፤ እና

ቀ) የአካባቢው ማህበረሰብ ያለው ተሳትፎ በገንዘብ መጠን...........3 ነጥብ ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ሀ ለመንገድ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት የአስተዳደር ሁኔታና የህዝብ ብዛት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ህዝብ ብዛት ነጥብ} = 100 * \left\{ \frac{\text{ጠቅላላ የህዝብ ብዛት} - \text{ተጠቃሚ የሆነው የህዝብ ብዛት}}{\text{ጠቅላላ የህዝብ ብዛት}} * (7\%) \right]$$

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ መ ለመንገድ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት የመንገድ ጥግግት መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ዝርዝር ስሌት እንደሚከተለው ይሆናል፦

ሀ) ከ149.99 በታች..............10 ነጥብ፤

ለ) ከ150-199.99..................8 ነጥብ፤

ሐ) ከ200-249.99..................6 ነጥብ፤

መ) ከ250-299.99....................4 ነጥብ፤

ሠ) 300 በላይ.......................2 ነጥብ፤ ይሆናል፤

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ መ ለመንገድ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት የመንገድ ጥግግት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{የመንገድ ጥግግት በ1000 ኪ.ሜ ስኩየር} = \left[ \left\{ \frac{\text{የመንገድ ርዝመት(በኪ.ሜ)}}{\text{የቆዳ ስፋት}} * 1000 \right] \right.$$

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሐ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለመንገድ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት ፕሮጀክቱ በአካባቢው ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ አመላካቾችም፦

ሀ) ለመሬት መንሸራተት ያለው ተጋላጭነት.........2.5 ነጥብ፤

ለ) መሬት መሸርሸር ያለው ተጋላጭነት................2.5 ነጥብ፤

ለ) በደን ላይ የሚደርሰው ጉዳት..........................2.5 ነጥብ፤

ሐ) በእርሻ መሬት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት...........2.5 ነጥብ፤ ይሆናል፤

8/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 7 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንገድ መሰረተ ልማት ፕሮጀክት ለመመደብ በ3 መስፈርቶች ድምር ውጤት 80 በመቶና ከዚያ በላይ ሲያሟላ የጠየቀው አካል በአገኘው የነጥብ ደረጃ ፕሮጀክቱን በቅድሚያ የሚያገኝ ሲሆን ውጤቱ ከዚህ በታች ከሆነ በአገኘው ውጤት ደረጃ መሰረት እንደቅደም ተከተሉ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

## 11. የመስኖ መሠረተ ልማት ፕሮጀክት

1/ የመስኖ መሠረተ ልማት ፕሮጀክት መመዘኛ መስፈርቶች፦

ሀ) በመስኖ መልማት የሚችል መሬት እና ውኃ፤

ለ) የህዝብ ብዛት፤

ሐ) በመስኖ ልማት የአርሶ አደሮች ተጠቃሚነት፤

መ) የህዝብ ፍላጎትና አስተዋጽኦ እና፤

ሠ) የድርቅ ተጋላጭነት ናቸው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሀ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለመስኖ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት በመስኖ መልማት የሚችል መሬት እና ውኃ መስፈርት 40 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ በመስኖ መልማት የሚችል መሬት መኖሩ ትኩረት በማድረግና ውሃን በዘላቂነት ጠብቆ መጠቀም እንዲቻል ተደርጎ መሰራት አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ለመስኖ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት በመስኖ መልማት የሚችል መሬት እና ውኃ መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = 100 * [\{\frac{(\text{በመስኖ መልማት የሚችል መሬት} - \text{ከዚህ በፊት የለማ መሬት})}{\text{የቆዳ ስፋት}}] * \text{ለነጥቡ ክብደት} (40\%)$$

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ለ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለመስኖ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት የህዝብ ብዛት መስፈርት 30 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ አመላካቾችም፦

ሀ) የመስኖ ግንባታ ተቋማትን የመገንባት አስፈላጊነት፤

ለ) ኢኮኖሚያዊ አዋጭነትን፤

ሐ) ለፕሮጀክቶች ዘላቂነት የህዝብ ተሳትፎ መኖሩ፤

መ) ለመስኖ ግብርና የሚመቹ አካባቢዎች መኖር ናቸው።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ለመስኖ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት የህዝብ ብዛት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = [100 * [\frac{(\text{የህዝብ ብዛት} - \text{በመስኖ ተጠቃሚ የሆነዉ ህዝብ ብዛት})}{\text{የህዝብ ብዛት}}]] * \text{ለነጥቡ ክብደት} (30\%)$$

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሐ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለመስኖ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት በመስኖ ልማት የአርሶ አደሮች ተጠቃሚነት መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ ለወጣቶች የስራ እድል መፍጠርን ትኩረት በማድረግ መሰራት አለበት።

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ለመስኖ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት በመስኖ ልማት የአርሶ አደሮች ተጠቃሚነት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = 100 * [\{\frac{\text{በመስኖ ልማት የአርሶ አደሮች ተጠቃሚነት}}{\text{በስራ እድሜ ክልል ለሚገኙ የህዝብ ብዛት}}] * \text{ለነጥቡ ክብደት} (10\%)$$

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ መ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለመስኖ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት የህዝብ ፍላጎት እና አስተዋፅኦ መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ ዝርዝር ስሌቱም፦

ሀ) የህዝብ ፍላጎት 3 በመቶ ሆኖ ተጠቃሚው ማህበረሰብ በደብዳቤ ፍላጎቱን ማረጋገጥ አለበት፤

ለ) የህዝብ አስተዋጽኦ 7 በመቶ ሆኖ ፕሮጀክቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ማህበረሰቡ የሚያደረገውን የጉልበት፣ የገንዘብ እና የሶስተኛ ወገን ጥያቄዎችን ለመፍታት ያለው ዝግጁነት መኖሩ መረጋገጥ አለበት፡፡

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሠ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለመስኖ መሠረተ-ልማት ፕሮጀክት የድርቅ ተጋላጭነት መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ አስፈላጊነታቸው የሚመዘነውም፦

ሀ) ከተለመዱ የዝናብ ግብርና ዘዴዎች በተጨማሪ በቂ ምርት ለማምረት፤

ለ) የምግብ እጥረት እንዳይከሰት ለማድረግ፣

ሐ) የውሃ ማስተዳደር ስልቶች ለመንደፍ ወይም የውሃ ማጠራቀሚያ ለመገንባት፤

መ) የማህበረሰቡን የኑሮ ደረጃ በመጠበቅ ኢኮኖሚያዊ መረጋጋትን ለማምጣት እና፤

ሠ) ዘመናዊ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች ለመጠቀምና ተዳራሽ ለማድረግ ናቸው፡፡

10/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 9 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመስኖ መሰረተ ልማት ፕሮጀክት ለመመደብ በ5 መስፈርቶች ድምር ውጤት 75 በመቶና ከዚያ በላይ ሲያሟላ የጠየቀው አካል በአገኘው የነጥብ ደረጃ ፕሮጀክቱን በቅድሚያ የሚያገኝ ሲሆን ውጤቱ ከዚህ በታች ከሆነ በአገኘው ውጤት ደረጃ መሰረት እንደቅደም ተከተሉ የሚስተናገድ ሆኖ ከ35.99 በታች ነጥብ የሚኖራቸው አካላት የማይፈቀድላቸው ይሆናል፡፡

## 12. የኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች

1/ የኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ፕሮጀክት መመዘኛ መስፈርቶች፦

ሀ) ዘላቂ የምርት ግብዓት አቅም፤

ለ) ማዕከላዊነት፤

ሐ) የመሰረተ ልማት አቅርቦት፤

መ) የመሬት አቅርቦት፤

ሠ) የመሬት አቀማመጥ፤

ረ) ሰላማዊና ማህበራዊ ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ እና፤

ሰ) የሰው ሀይል አቅርቦት ናቸው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሀ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ዘላቂ የምርት ግብዓት አቅም መስፈርት 20 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን የምርት ጥራት በከፍተኛ ሁኔታ ያሉበት መሆኑን ጭምር ተረጋግጦ መሰራት አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ለ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች የማዕከላዊነት መስፈርት 20 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን ዝርዝር ስሌቱም፦

ሀ) ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ምርቶች ለማቅረብ ቅርበት ያለው ቦታ 5 በመቶ፤

ለ) የአየር ትራንስፖርት ያለው ቀረቤታ 5 በመቶ፤

ሐ) ለዋና ከተማ ወይም ለወደብ ያለው ቀረቤታ 5 በመቶ እና፤

መ) የሚያስተሳስሩ መንገዶች ያለው ቀረቤታ 5 በመቶ፤ ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሐ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች የመሰረተ ልማት አቅርቦት መስፈርት 20 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን ዝርዝር ስሌቱም፦

ሀ) ትራንስፖርት መሰረተ ልማቶችን አቅርቦት 5 በመቶ፤

ለ) የተሻለ የኤሌክትሪክ ኃይል አቀርቦት 10 በመቶ፤

ሐ) የውሀ አቀርቦት 5 በመቶ፤ ይሆናል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ መ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች በተለይም ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ለመገንባት የመሬት አቅርቦት መስፈርት 20 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን ዝርዝር ስሌቱም፦

ሀ) የመሬት አቅርቦት (በሄክታር) ከ50,000 እና በላይ........20 ነጥብ፤

ለ) የመሬት አቅርቦት (በሄክታር) 49,999 እስከ 30,000....15 ነጥብ፤

ሐ) የመሬት አቅርቦት (በሄክታር) 29,999 እስከ 15,000....10 ነጥብ፤

መ) የመሬት አቅርቦት (በሄክታር) ከ14,999 በታች............5 ነጥብ፤ ይሆናል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሠ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች የመሬት አቀማመጥ መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን የመሬቱ አቀማመጥ ከጎርፍ፣ ከመሬት መንቀጥቀጥ እና ከእሳተ ገሞራ መራቁ ተረጋግጦ መሰራት አለበት፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ረ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ሰላማዊና ማህበራዊ ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ መስፈርት 5 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን በተለይም የኢኮኖሚ ዞን ሲቋቋም ሰላምና ደህንነቱ በዘላቂነት የተጠበቀ መሆኑን እየተረጋገጠ መሰራት አለበት፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሰ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች የሰው ሃይል አቅርቦቱ መስፈርት 5 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን በተለይም የኢኮኖሚ ዞን ሲቋቋም በከፍተኛ ሁኔታ የሰው ሃይል አቅርቦት ያለበት አካባቢ መሆኑ እየተረጋገጠ መሰራት አለበት፡፡

9/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 8 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ፕሮጀክት ለመመደብ በ7 መስፈርቶች ድምር ውጤት 90 በመቶና ከዚያ በላይ ሲያሟላ የጠየቀው አካል በአገኘው የነጥብ ደረጃ ፕሮጀክቱን በቅድሚያ የሚያገኝ ሲሆን ውጤቱ ከዚህ በታች ከሆነ በአገኘው ውጤት ደረጃ መሰረት እንደቅደም ተከተሉ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

## 13. የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት

1/ የእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት መመዘኛ መስፈርቶች፦

ሀ) የእንስሳት ብዛት እና የዓሣ ዕምቅ ሃብት፤

ለ) ከእንስሳት የሚገኙ ምርቶች፤

ሐ) የእንስሳት መኖ አቅርቦት፤

መ) የእንስሳት ጤና አገልግሎትን ማሻሻል፤

ሠ) የአየር ንብረት እና፤

ረ) የመሰረተ ልማት ተጠቃሚነት ናቸው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሀ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክቶች የእንስሳት ብዛት እና የዓሣ ዕምቅ ሃብት መስፈርት 40 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን የእንስሳቱ ብዛት በአይነት ጭምር ተረጋግጦ መሰራት አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ለእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት የእንስሳት ብዛት እና የዓሣ ዕምቅ ሃብት መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = 1500 * \left\{ \frac{\{\text{የእንስሳት ብዛት በአይነት}\}}{\{\text{የክልሉ የእንስሳት ብዛት በአይነት}\}} \right.$$

$$\text{ለዓሣ ሃብት ልማት ነጥብ} = \left[100 * \left\{ \frac{\{\text{ለዓሣ እርባታ ምቹ የሆነ የውሃ ሽፋን መጠን በሄ/ር}\}}{\{\text{ለዓሣ እርባታ ምቹ የሆነ የክልሉ የውሃ ሽፋን መጠን በሄ/ር}\}} \right.\right] * \text{ለነጥቡ ክበደት}(40\%)$$

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ለ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክቶች ከእንስሳቱ የሚገኙ ምርቶች መስፈርት 20 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ ከእንስሳቱ የሚገኘው ምርት ብዛትና ጥራት ጭምር ተረጋግጦ መሰራት አለበት፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ለእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት ከእንስሳቱ የሚገኙ ምርቶች መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$\text{ነጥብ} = 700 * \left\{ \frac{\{\text{ከእንስሳት የሚገኙ ምርቶች በአይነት}\}}{\{\text{ከክልሉ እንስሳት የሚገኙ ምርቶች በአይነት}\}} \right.$$

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሐ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክቶች የእንስሳት መኖ አቅርቦት መስፈርት 15 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ የተፈጥሮ ግጦሽ፣ የሰብል ተረፈ ምርት እና ከኢንዱስትሪ ለመኖነት የሚያገለግሉ ተረፈ ምርቶች የሚገኙባቸው አካባቢዎች መኖራቸው ጭምር ተረጋግጦ መሰራት አለበት፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ መ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክቶች የእንስሳት ጤና አገልግሎትን ማሻሻል መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ የአገልግሎት መሻሻል በሰው ሃይል፣ በቁሳቁስ፣ በክሊኒኮች ግንባታ ተደራሽነትና የገበሬዎችን ገቢ ማሳደጉ እየተረጋገጠ መሰራት አለበት፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 ለእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክት የእንስሳት ጤና አገልግሎትን ማሻሻል መስፈርት የሚያስገኘው ነጥብ በሚከተለው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

$$ነጥብ = 700 * \left\{ \frac{\{ክሊኒክ ኖሯቸው አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ቀበሌዎች ብዛት\}}{\{በክልሉ ክሊኒክ ኖሯቸው አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ቀበሌዎች ብዛት\}} \right.$$

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሠ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክቶች የአየር ንብረት አይነቶች መስፈርት 5 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ ፕሮጀክቶቹ ለአየር ንብረቱ ተስማሚ መሆናቸው ጭምር እየተረጋገጠ መሰራት አለበት፡፡

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ረ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለእንስሳት ሀብት ልማት ፕሮጀክቶች የመሰረተ ልማት ዝርጋታ መስፈርት 10 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሆኖ፦

ሀ) 5ቱን የመሰረተ-ልማት አይነቶች ማለትም መንገድ፣ ቴሌ፣ ውሃ፣ መብራት እና የአውሮፕላን ማረፊያ በ40 ኪሎ ሜትር ውስጥ የሚያገኙ አካባቢዎች 10 ነጥብ፤

ለ) 4ቱን መሰረተ-ልማቶች የሚያገኙ አካባቢዎች 8 ነጥብ፣

ሐ) 3ቱን መሰረተ ልማቶች የሚያገኙ አካባቢዎች 6 ነጥብ፣

መ) 2ቱን መሰረተ-ልማቶች የሚያገኙ አካባቢዎች 4 ነጥብ እና፤

መ) 1 መሰረተ-ልማት የሚያገኝ አካባቢ 2 ነጥብ እንዲሰጣቸው እየተደረገ መሰራት አለበት፡፡

11/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 10 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለእንስሳት ሃብት ልማት ፕሮጀክት ለመመደብ በ6 መስፈርቶች ድምር ውጤት 75 በመቶና ከዚያ በላይ ሲያሟላ የጠየቀው አካል በአገኘው የነጥብ ደረጃ ፕሮጀክቱን በቅድሚያ የሚያገኝ ሆኖ ከ44.99 በታች ነጥብ የሚኖራቸው አካላት የማይፈቀድላቸው ይሆናል፡፡

## 14. የቱሪዝም ልማት ፕሮጀክት

1/ የቱሪዝም ልማት ፕሮጀክት መመዘኛ መስፈርቶች፦

ሀ) የቅርሱ ወይም መስህቡ ወይም መዳረሻው ልዩ ገጽታና ዋጋ፤

ለ) የቅርሱ ወይም መስህቡ ወይም መዳረሻው በዙሪያው ያሉ የለሙና ወደፊት መልማት የሚችሉ ቅርሶች ብዛት እና፤

ሐ) ለሁሉም የመሰረተ ልማት አይነቶች ያለው ቅርበትና የመተሳሰር አመቺነት ናቸው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሀ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለቱሪዝም ልማት ፕሮጀክቶች የቅርሱ ወይም መስህቡ ወይም መዳረሻው ልዩ ገጽታና ዋጋ መስፈርት 35 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን ዝርዝር ስሌቱም፦

ሀ) ታሪካዊ ዋጋ (5%)፤

ለ) ባህላዊ ዋጋ (5%)፤

ሐ) ስነ-ውበት ዋጋ (5%)፤

መ) ሳይንስና ምርምር ዋጋ (5%)፤

ሠ) መንፈሳዊ ዋጋ (5%)፤

ረ) ስነ-ህንጻ ዋጋ (5%)

ሰ) ስነ-ህይወት ዋጋ (5%)፤ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ለ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለቱሪዝም ልማት ፕሮጀክቶች የቅርሱ ወይም መስህቡ ወይም መዳረሻው በዙሪያው ያሉ የለሙና ወደፊት መልማት የሚችሉ ቅርሶች ብዛት መስፈርት 25 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን ዝርዝር ስሌቱም፦

ሀ) 5 እና በላይ የተፈጥሮ ቅርሶች መኖር (10%)፤

ለ) 10 እና በላይ የባህላዊ ቋሚ ቅርሶች መኖር (10%)፤

ሐ) 5 እና በላይ ባህላዊ የማይዳሰሱ ቅርሶች መኖር (5%)፤ እየተሰጣቸው መሰራት አለባቸው።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሐ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለቱሪዝም ልማት ፕሮጀክቶች ቅርሱ ወይም መስህቡ ወይም መዳረሻው ለሁሉም የመሰረተ-ልማት አይነቶች ያለው ቅርበትና የመተሳሰር አመቺነት በ10 ኪሎ ሜትር ውስጥ ሆኖ መስፈርቱ 40 በመቶ ነጥብ ክብደት የሚሰጠው ሲሆን ዝርዝር ስሌቱም፦

ሀ) የመንገድ መሰረተ ልማት ከሚገኝበት ስፍራ ያለው ርቀት (10%)፤

ለ) የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ከአለበት ስፍራ ያለው ርቀት (10%)፤

ሐ) የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ከሚገኝበት ስፍራ ያለው ርቀት (10%) እና፤

መ) የአየር ማረፊያ ከሚገኝበት ስፍራ ያለው ርቀት (10%)፤ ይሆናል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለቱሪዝም ልማት ፕሮጀክት ለመመደብ በ3 መስፈርቶች ድምር ውጤት 80 በመቶና ከዚያ በላይ ሲያሟላ የጠየቀው አካል በአገኘው የነጥብ ደረጃ ፕሮጀክቱን በቅድሚያ የሚያገኝ ሆኖ ከ49.99 በታች ነጥብ የሚኖራቸው አካላት የማይፈቀድላቸው ይሆናል፡፡

## 15. <u>ልዩ ሁኔታ</u>

1/ በዚህ መመሪያ ለልዩ ልዩ ተቋማት የተገለጸው የፕሮጀክት መደልደያ ቀመር መመዘኛ መስፈርቶች ቢኖሩም ተቋማት እንደ አስፈላጊነቱ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በልዩ ሁኔታ በመስተዳድር ምክር ቤቱ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው በማድረግ ግንባታዎችን ማከናወን ይችላሉ፡፡

2; በዚህ አንቀጽ ንዑስ 1 መሰረት መስተዳድር ምክር ቤቱ ውሳኔ ሲሰጥ የተበታተነ አሰፋፈር ያለባቸውን አካባቢዎች፣ ፕሮጀክቶቹ ለክልሉ ህዝብ ጥቅም የሚያስገኘውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጠቀሜታዎች ግንዛቤ ውስጥ ያስገባል፡፡

# ክፍል ሦስት

# በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለመገንባት የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

## 16. በጦርነት በተጎዱ አካባቢዎች የሚገነቡ ፕሮጀክቶች የአሰራር ሥርዓት

1/ በጦርነቱ የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለማቋቋም የሚገነባው ፕሮጀክት የደረሰውን ውድመትና ኪሳራ መሰረት በማድረግ ይሆናል፤

2/ በጦርነቱ የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለማቋቋም ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች በመንግስት የሚመደብ በጀት እና ከተለያዩ አካላት የሚገኙ ድጋፎች ለክልል ሴክተር መስሪያ ቤቶች በተቀመጠው መስፈርት በመከፋፈል የሚከናወን ይሆናል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለሴክተሮች የሚደረገው የበጀት ድልድል በአማራ ክልል በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎች መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፈንድ ጽህፈት ቤት ቦርድ የሚከናወን ይሆናል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ቦርዱ የበጀት ድልድል ሲያደረግ በልዩ ሁኔታ መካተት የሚገባቸውን ተቋማት (ተጋላጭ እና ተጎጅ የሆኑ ማህበረሰብ ክፍሎችን) ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ይሆናል፤

5/ በጦርነቱ የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለማቋቋም የሚገነባው ፕሮጀክት በዚህ መመሪያ ክፍል 2 በተቀመጡ ጥቅል እና በመደበኛ የፕሮጀክቶች መደልደያ መስፈርት በተለየ አግባብ የሚፈጸም ይሆናል፤

## 17. በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለመገንባት የሚሰሩ ፕሮጀክት መመዘኛ መስፈርቶች፡-

1/ ለሴክተር መስሪያ ቤተቶች ለሚደረገው የበጀት ድልድል መመዘኛ መስፈርቶች እና ነጥብ ክብደት በመቶኛ፦

ሀ) በጦርነት እና በግጭት የደረሰ ጉዳት መጠን ቁሳዊ ውድመት (35%)፤

ለ) በጦርነት እና በግጭት የደረሰ ሰብአዊ ጉዳት (15%)፤

ሐ) ሴክተሩ ተጠቃሚ የሚያደርገው የህብረተሰብ ብዛት (30%)፤

መ) ሴክተሩ በሚተገብረዉ ፕሮጀክት በመደበኛም ሆነ በረጅ ድርጅቶች የሚኖረዉ መቀናጆ የበጀት አስተዋጽኦ (10%)፤

ሠ) ባለፈው በጀት ዓመት በፈንድ ፅ/ቤቱ የተመደበለት በጀት አጠቃቀም (10%)፤ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለመገንባት ለሴክተሮች በጀት የሚደለደለው በሚከተለው ቀመር ተሰልቶ ይሆናል፡፡

በጀት ለመደልደል= <u>ሴክተሩ በመመዘኛ መስፈርቶቹ ከመቶ ያገኘዉ ውጤት X ለድልድል የቀረበዉ በጀት መጠን</u>

አጠቃላይ ሴክተሮች በመመዘኛ መስፈርቱ ያገኙት ድምር ውጤት

3/ በጦርነት ለተጎዱ ወረዳዎች ለሚደረገው የበጀት ድልድል መመዘኛ መስፈርቶች እና ነጥብ ክብደት በመቶኛ፦

ሀ) በጦርነት እና በግጭት የደረሰ ጉዳት መጠን ቁሳዊ ውድመት (45%)፤

ለ) በጦርነት እና በግጭት የደረሰ ሰብአዊ ጉዳት (20%)፤

ሐ) ለመልሶ ማቋቋ እና ግንባታ ያሰባሰበዉ ሃብት መጠን (30%)፤

መ) ሊያሰራ የሚችል የፀጥታ ሁኔታ መኖሩ (5%)፤ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ለይ የተገለጸው ቢኖርም በሴክተሩ በተመረጠዉ ወረዳ የሚተገበረዉ ፕሮጀክት በጦርነት ወይም በግጭት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የወደመ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተገለጸው ቢኖርም በ3R-4CACE እና UNDP Peace Support Facility ፕሮጀክት የታቀፉ እና በሌሎች ፕሮጀክቶች በመልሶ ማቋቋም እና ግንባታ ስራዎች ተጨባጭ ድጋፍ እየተደረገላቸዉ ያሉ ወረዳዎች ለውድድር የሚቀርቡ አይሆኑም፡፡

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### የፕሮጀክት በጀት መደልደያ ታሳቢዎች

1/ በአንድ ዓመት የሚጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ የሚያስችል ሙሉ በጀት እንዲመደብላቸው ይደረጋል፤

2/ በሁለት እና ከዚያ በላይ ዓመታት የሚጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ለየበጀት ዓመቱ በየውላቸው መሰረት በጀት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፤

3/ በ25 እና 5 ዓመታት የአሻጋሪ ዕድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅዶች መሰረት የቀዳሚ ዘርፎች ልማት ማለትም ለአምራች ኢንዱስትሪ፣ ለዘመናዊ ግብርና፣ ለማዕድን ሃብት፣ ለትምህርት እና ለጤና ፕሮጀክቶች ቅድሚያ በመስጠት በጀት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፤

4/ በተመሳሳይ በ25 እና 5 ዓመታት የአሻጋሪ ዕድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅዶች መሰረት ለኢኮኖሚ ልማት (ለቱሪዝም፣ ለንግድና ገበያ ልማት፣ ለትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ እና ለኮንስትራክሽን)፣ ለማህበራዊ ልማት፣ ለከተማና የገጠር ልማት፣ ለአካባቢ ጥበቃና ልማት፣ ለልማት አቅሞች (የሰው ኃይል ስልጠና፣ ለቴክኖሎጅ፣ ለመሰረተ ልማትና ለመዋዕለ ንዋይ) እና ለስርዓታትና ልማት ከቀዳሚ ዘርፎች ልማት በመቀጠል እንደ ቅደም ተከተላቸው በጀት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፤

5/ ማንኛውም ፕሮጀክት በሚቀርብበት ወቅት የ25 እና 5 ዓመታት የአሻጋሪ ዕድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅዶችን መሰረት በማድረግ በአዲስ ከተዘጋጀው የፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ዝርዝር ወጭ መሆን የለበትም፣

## 18. የፕሮጀክት በጀት

1/ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 18 የተገለጹ የፕሮጀክት በጀት መደልደያ ታሳቢ ሁኔዎች እንደተጠበቁ ሆነው የክልሉ መንግስት ከሚመደበው ዓመታዊ በጀት በ2018 25% እንዲሁም በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ እስከ 35% በጀት ለፕሮጀክት እንዲውል ያደርጋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በህብረተሰቡ ተሳትፎ ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ማህበረሰቡ በጉልበት፣ በዓይነት፣ በእውቀት እና በገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግበት አሰራር ይዘረጋል፡፡

## 19. የመረጃ አጠቃቀም

1/ ለዚህ መመሪያ አገልግሎት የሚውል ማንኛውም መረጃ በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ መረጃዎችን የማደራጀትና የመተንተን ስልጣን በተሰጣቸው ተቋማት ሲረጋገጥ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም በጉዳዩ ላይ በተደረገ ጥናት የሚቀርብ መረጃ በሚመለከተው አካል እየተረጋገጠ ለመመሪያው ግብዓት ሊሆን ይችላል።

## 20. የመተባበር ግዴታና ተጠያቂነት

1/ ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፤

2. ማንኛውም ሰው የዚህን መመሪያ ድንጋጌ ተላልፎ ቢገኝ እንደየአግባቡ አስተዳደራዊ፣ ፍትሐብሔራዊና የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርበታል።

## 21. መመሪያውን የማሻሻል ስልጣን

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ም/ቤት አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል።

## 22. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ወደ ትግበራ የገባ ፕሮጀክት ሲሠራበት በነበረው ሥርዓት መሠረት ፍፃሜ ያገኛል።

## 23. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ባህር ዳር**

**ቀን 30/4/2018 ዓ.ም**

**አረጋ ከበደ ለጋስ**

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ-መስተዳድር**